*Association Suisse de Soutien*
à l'Union des Forces
Démocratiques Ethiopiennes

*Schweizer Unterstützungsverein*
für die vereinigten
demokratischen Kräfte Äthiopiens

**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት**
**የድጋፍ ማህበር በስዊስ**
Case postale 274, 1211 Geneva 4

መስከረም 17 ቀን 1999 ዓ.ም.

## መልዕክት ከህብረት ድጋፍ ማህበር በስዊዘርላንድ (ህድማስ)

*በስዊዘርላንድ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ*

ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበትን አስፈሪና አስከፊ ሁኔታ በየእለቱ ሥራዬ ብሎ የማይከታተልና ያልተረዳ ፣ ይህም የማይመለከተው፣ የማያሳስበውና የማያስፈራው ኩሩ ኢትዮጵያዊ፣ የትም ይሁን የት ይኖራል ብሎ ማሰብን አንደፍርም::

ተከብሮ የቆየው የሀገራችን ኢትዮጵያ ምንነትና ማንነት፣ ኩራትና ክብር፣ ህልውናና ታሪክ መደፈር የማያንገበግበውና እናት ሀገር ለልጆችዋ የምታሰማው የጣር ጥሪ እስከ አጥንቱ ዘልቆ የማይሰማው ሀገሩን ወዳድ ኢትዮጵያዊ አይኖርም:: ህዝቡን የናቁና ያዋረዱ ዕብሪተኞች የሚያኪያሂዱት ዝርፊያና ስራዬ ብለው ህዝብን የማዋረድ ተግባራቸው አንጀቱን ያላሳረረው ፣ የህዝቡ በበሽታ መጎሳቀል፣ በድህነት አረንቋ ውስጥ መዳከር፣ በድንቁርናና በሁዋላ ቀርነት ማጥ ውስጥ መማሰን ያላንገበገበው፣ ይህ ኩሩ ህዝብ እንዳልሆነ ሆኖ መገኘቱ ብግን አድርጎ ያላሳረረው ኢትዮጵያዊ አይኖርም ቢባልም እውነት ነው:: ቢኖሩ ለነዚህ ሁሉ በደሎች ተጠያቂ የምናደርጋቸው፣ አገር አጥፊው እኩይ ቡድንና ግብረ በላ ጋሻ ጃግሬዎቹ ብቻ ናቸው የሚሆኑት::

ለብቻ መትከንከን፣ መብገንና ማረር ብቻም አይደል፣ ኩሩው ኢትዮጵያዊ በያለበት በዚህ ስርዓት ላይ ያሳደረውን ከፍተኛ ጥላቻ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ በአደባባይ ገልጿል:: መወገድ ያለበት መሆኑንም ካመነ የስርዓቱን እድሜ ያህል ዘመን አስቆጥሯል:: ለብቻውም ይሁን ተደራጅቶ አምርሮ በመሰለውና ባመቸው ዘዴ ሁሉ ታግሎታል፣ ዛሬም እየታገለው ነው::

ያለቅጥ ሲያፈሉት... ቡና እንኩዋ ገንፍሎ፣
ያጠፋል እሳቱን ... ደመኛዬ ብሎ::

ነውናም ትነስም ትብዛ ሁሉም በያለበት የየድርሻውን፣ የየችሎታውን ይሞክራል::

እኛ ኢትዮጵያውያን አገር ወራሪንና ድንበር ገፊን የውጭ ጠላት ደጋግሞ የመቅጣት ጀግንነት፣ አገር - ህዝብ የሚባሉ ክቡራን ጌጦቻችን እንዳይነኩብን ስሱነት፣ ሲነኩብን እንደ ተርብ የመናደፍ ቁጡነት፣ ዳር ድንበርን በደም ጠብታ አስከብሮና ከልሎ የማቆየቱ ጥበብና ክህሎት በደማችን ውስጥ ይመላለሳል ብለን የምንኮራ ዜጎች ነን::

የታሪካችን ንፅህና ጥራቱ የሚጎላውና የበለጠ የሚያኮራን ደግሞ፣ እርስ በርሳችን እንድንጠፋፋ ተደጋግሞ ቢሴርብንምና ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በምድር ላይ እንዳትኖር ተደጋግሞ ቢዶለትም፣ በብሄር፣ በብሄረ-ሰብ፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት ልዩነት ጎራ ለይተን እርስ በርስ ያልተፋጀን፣ ሀገሪቱን እንደ ተረከብናት ልናቆያት የጣርንና ሴራዎቹን ደጋግመን ያመከንን ህዝቦች የመሆናችን ሃቅ ሲወሳ ነው:: የጀግኖች እናት-አባቶቻችን አምሳያ የሌለው ገድል እኛን ልበ ሙሉ ማድረጉ፣ የአኩሪ ታሪክ ባለቤትነትን ፀጋ ማጎናፀፉና በተለይ ለዛሬውም ትግላችን ስንቅም-ብርታትም መሆኑ ለእኛ ቅርሳችን ነው::

ተከታዩም ትውልድ አልሆኑኝም ያላቸውን ሦስት አገዛዞችን በተከታታይ ሳያቋርጥ የመታገሉ ብርታት የሚያኮራንን ያህል፣ ሀገር ወዳድነቱና ህዝባዊ ፍቅሩ፣ ድፍረቱና ቆራጥነቱ፣ አሻፈረኝ ባይነቱና ቁጡነቱ የሚያስከብረን ነው:: የትም እንሁን የት፣ ሀገር - ህዝብ - ሰንደቅ ዓላማ ምን ጊዜም ከልባችን የማይጠፉ ፅላቶቻችን የመሆናቸው ፀጋ እንደመለያ/መታወቂያነት ከየግንባራችን የመለጠፉም እውነታ ክብራችን መሆኑም አያጠያይቅም::

ዛሬ ወደ ውስጣችን ስንመለከት ግን በእጅጉ የሚያሳስበንና ተጠቂም እንድንሆን ያደረገን አንድ ትልቅ ችግር እንዳለብን እንገነዘባለን:: ይህንን ችግራችንንም የመወያያ አርዕስታችን ካደረግነው ብዙ ጊዜ ሆኖናል::የሚያሳስበን፣ ባለ ታሪክነታችን ላይ ጥላ ሊያጠላ መሆኑ የሚያነጋግረን፣ በዚህ ዘመን ላይ ያለን የኩሩ ታሪክ ወራሾች የሚጎድለን ትልቁ ቁም ነገር ምን እንደሆነ ለመረዳት ሩቅ መጓዝ፣ መፅሐፍ ማገላበጥ ወይም አማካሪ ፍለጋ መማሰንን አይጠይቀንም:: ህዝቡ ነግሮናል::

ለእኩልነት፣ ለዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶቻችን መከበር ፣ ለህግ የበላይነት መስፈን፣ ለእድገትና ለብልፅግና ያደረግናቸው ዘመናት ያስቆጠሩ ትግሎቻችንን ገና ዳር አላደረስናቸውም:: አሜከላውን ከመርገጫችን፣ ቆንጥሩን ከቋንጃችን፣ ጅንግላውን ከጫንቃችን እስከወዲያኛው ከልተን፣ መከራችን አብቅቶ እኛው ለኛው ልንሆንና ህልም-ራዕያችን ፍቺ እንዲያገኙ አልበቃንም::

ለሀገር ውርደትና ጥፋትን፣ ለህዝቡ ድንቁርናን፣ ኋላ-ቀርነትን፣ ድህነትንና ስቃይ-መከራን ደግሰውና የሞት ቀጠሮ ግባቸው አድርገው በኛው ላይ የዘመቱቱ ጥቂት ሃይላት፣ ሴራቸው ውል እንዲይዝላቸው ያበቃቸው፣ ያንንም እንዲተገብሩ ያስቻላቸው መስማማት፣ መተባበር፣ መቻቻልና መደጋገፍ መቻላቸው ብቻ ነው:: ድፍረት ያገኙት ሠናይ ዓላማ ኖሯቸው ሳይሆን፣ እብሪቱም አልበርድላቸው ብሎ እንደ ጀመሩ ቀጥለውበት ያሉትም የተለየ ብልህት፣ የተለየ ጀግንነት ወይም የተለየ ተፈጥሮ ኖሯቸው ሳይሆን፣ ህብረታቸው ብቻ ጉልበት ሆኗቸው መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም:: ተፈጥሮ ለዚህ አጥፊ ቡድን አባላት ብቻ ለይታ የቀባችው ልዩ ቅብዓት ቢኖራት፣ ህዝብን ያህል ትልቅ ነገር የመናቅ ድፍረትን፣ የበላበትን ወጭት የመስበር ያግድም-አደግ ብልግናን፣ ህሊና ቢስነትንና ሌላም ሌላም እርጉም ባህሪያትን ሁሉ አሰባስባ ያከናነበቻቸው መሆኗና እነዚሁ ተፈላልገው እንዲገናኙ ጥበቡን መለገሷ ብቻ ነው:: “ወል ፈካቲን ወል በርባዲ” ይላል ያገር ልጅ በኦሮምኛ ሲተርት...ምን ለምን አብረህ አዝግም ለማለት::

እንደ ጨው ዘር ተበትነን በየትኛውም የዓለም ጉራንጉር የምንገኝ ኢትዮጵያውያን፣ ሀገር ወዳድነቱ ሳያጥጠን፣ ህዝባዊ ፍቅሩ ብድር ሳያስኬደን፣ ቆራጥነቱና ድፍረቱ ሳያንሰንና ትኩስነቱም በርዶ የፍርሃት ቆፈን ሳይሸመቅቀን፣ ሀገር ያህል ነገር ሲናድ የኛው ኢላማውን የሳተው የትግላችን ቅኝት እኛኑ ጠላልፎ ሲያናችፈን እንገኛለን:: የሂደቱም አኳሁዋን ውሉን ስቷልና አውዳሚው የሀገር ብል-ጥንጣን እየጀገነ፣ ይበልጥም እየጎለበተ እንዲሄድ ሳናውቅ ረድተነዋል:: ማራገፍም አቅቶን፣ ጥቃት ባጎበጠው ጫንቃችንም እነደተሸከምነው ወደ ሁለተኛው ሺህ ዘመን ልናሸጋግረው መባቻው ላይ ደርሰናል:: አገር አጥፊው “በገድሉ” ጉሮወሸቤውን፣ እኛም ምርጥ የሀገር ኩራቶቻችንን እየገበርን፣ የወጣት ጭዳም እያቀረብንና አንጀታችን እንደቆሰለ አስራ አምስት ዘመናት ቀጠርን::

ተግባር በፈተነው ማህበራዊ ክንዋኔ አበው ያቆዩልንን ምሳሌያዊ አነጋገሮች :- የድር ማበር አንበሳን ያህል ጉልበታም መጠፈር መቻሉን፣ አንድን ብርቱ ሁለት ያበሩ ኮስማኖች ልክ ማስገባት መቻላቸውን፣ እኒያ ጥቃቅን የጤፍ ፍሬዎች ተዳምረው እንጀራ ሲሰሩ ነፍስ አድን መሆን መቻላቸውን ፣ ፊቱ በጥፊ ሲቃጠል በእጁ ያልመከተ፣ መልሶም ያላጣፉ በዱላ ሲነረት መዋሉን፣... ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ የምናስታውስ፣ ነገር ግን በተቃራኒው የምንሰራ እዚህ ዘመን ላይ ያለን ወገኖች የጎደለን ይኸው ከምሳሌዎቹ ማግኘት ይገባን የነበረው ትምህርት ነው::

በመካከላችን ዛሬ መሰበክ ያለበት የጥላቻ ፖለቲካ መሆን አይደለም የሚገባው:: ዛሬ ዘመቻውና መናቆሩ በአንድ ጎራ ውስጥ ባለነውና የእምዬ ኢትዮጵያን ፀሎት በአንድ ቃና በምንደግም፣ ሀልም-ራዕያችን፣ መነሻ መድረሻችን አንድ በሆነው ወገኖች መካከል አይደለም መሆን የነበረበት:: ዛሬ ጦር መሰበቅ ያለበት ትላንት የቀምንበቱን አያስታውሰን፣ እሱኑ እያስታመምን የዛሬውን በረሳን፣ ነገር ግን የዛሬው ፈተና ያን ቅንጦት ባልሰጠን ወገኖች መካከል አይደለም መሆን ያለበት:: ዛሬ ግብግቡ እኛው በኛው ሆኖ እርስ በርስ በመጠላለፍ ተያይዞ ለመውደቅና ለአጥፊዎቹ የተመቻቸ የግልቢያ ሜዳ በማለስለስ ላይ አይደለም መሆን የሚገባው:: የዚህን ሁሉ አጓጉል አካሄድና እያስከተለ ያለውን ትርምስ አገር ታስተውላለች፣ ታሪክም ይዘግበዋል::

ከህዝቡ ተርታ የመሰለፉ ምርጫ ፈጠ ከመጣ ቆይቷል:: ሀገርን የማዳኑ ሀላፊነትና ግዴታ ለማንም አሻግረው የማይለቱት፣ ለማንም በወኪል የማይሰጡት፣ በይደርልኝም ወደ ጉራንጉር የማይሸጉጡት ወይም በድርጅት ተዋቅረው ለሚታገሉ ብቻም የማይተዉት፣ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግልና የጋራ ተግባር ነው ብለን እናምናለን::

ድርጅቶች የትግል ማማከያ/ማቀናጃ መድረኮቻችን እንጂ ነገረ ፈጆቻችን እንዳይደሉ የምናውቀውን ያህል ያለያንዳንዳችን አለሁ ባይነትና ተሳትፎ፣ አገዛና ትብብር ጉልበት-ጥንካሬ እንደማይኖራቸውም የእስከ ዛሬው ትግል በበቂ አስተምሮናል ባዮች ነን :: መግቢያው ላይ የጠቀስነው ቁም ነገር እውነት ከሆነ፣ እያንዳንዳችን የየመክሊታችንን ልናዋጣ እንደሚጠበቅብን፣ አገርና ህዝብ አደራ እያሉንም መሆኑን ማስታወሱ ተገቢ ነው እንላለን:: ይህን ሀብረት ልናገኝ፣ ለአንድ አገር ጉዳይ በአንድ ላይ ሆኖ፣ መክሮ፣ ተሰማምቶና ተማምኖ ሀገርን በማዳኑ ትግል የየድርሻችንን ልናበረክት እንችል ዘንድ ነው፣ ሁላችንን ሊያሳስብ፣ ሊያሰባስብና ሊያሳብር የሚችል የጋራ መድረክ አስፈላጊነትን ሀሳብ በስዊዘርላንድ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ልናካፍል የፈለግነው::

እኛ ኢትዮጵያውያን ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ ፖለቲካ እንደ ኮሬንቲ ተፈርቶ፣ እያንዳንዱ በራሱ ዙሪያ ግርግም ሰርቶና እርስ በርስ ተፈራርቶ የሚኖርበት ምቾት ውስጥ አይደለም:: በመሰላቸው መልክ ተደራጅተው፣ ይህንን ለማንም የማይለጋ የትውልድ ድርሻ፣ ሀላፊነት ተሸክመው ለሚታገሉ ሀይላትም የየድርሻችንን ሳናዋጣና የሚጠበቅብንን ሳናደርግ እንደ ተቀማጭ- ሰማይ-ቅርቡ ተረበኛና ዳገት ቁልቁለቱ ሁሉ ሜዳ ሆኖ እንደሚታየው ሰነፍ፣ ማማረርና ማላዘን ብቻ ከሆነ ተሳትፎአችን፣ በእውነትም ለኢትዮጵያ ጎህ የመቅደዱ ተስፋ ይራዘማል:: መከራችንም በራሳችን ድርጊት የተነሳ ማለቂያ አይኖረውም::

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እራሱን ካላሳነሰ፣ እኔ ድርሻ የለኝም ካላለ፣ ግዴታውን ለሌላ አሳልፎ ካልሰጠ በቀር፣ ሀኬተኛም ካልተሆነና በተለይም ለሀገር-ወገን ልቅሶ ቀዳው ደንድኖ፣ በልቶና ጠጥቶ ባደረ ብቻ ርካታ ተሰምቶት ቁም ነገር ካልከዳው በቀር፣ ለሀገር ማዳን ርብርቦሹ ልዩ የሆነ የራሱ አስተቀፅዖ ይኖረዋል::

ለነፃነት፣ ለመብት፣ ለሀገርና ለህዝብ መስዋዕት መክፈል ይገባል ሲባልም የግድ ከእያንዳንዱ ደም - ህይወትን መጠየቅ እንዳልሆነ ማስታወሱ ተገቢ ነው:: የሞቀ ቤት ውስጥ እየተኖረም፣ የተለመደ ምቾት

ሳይጓደልም፣ ቤተ-ሰብ ሳይበተንም ሆነ የተጀመረ እቅድ ሳይስተጓጎል፣ ለአገርና ለህዝብ ትንሽ-ትንሽ መቸገር ይቻላል:: ይህም መስዋዕትነት ነው:: የአገርን በደልና የወገንን ስቃይ አንጀት ውስጥ አስገብቶ እርር ድብን ማለት ራሱ ቁም ነገር ነው፣ በዚያው አያበቃምና::

ኢትዮጵያውያን እንደ ምርጫ-ዝንባሌያቸው ተደራጅተው ከሚታገሉባቸው ድርጅቶች፣ የድርጅት ስብስቦች/ህብረቶች/ጥምረቶች/ግንባሮች አንዱ ለሆነው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሀይሎች ህብረት (ህብረት) ደጋፊ የሆንን በስዊዘርላንድ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን፣ እኛም እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአለንበት ሆነን ላገር ልጆች መሰባሰብና ወደ ሀገር ጉዳይ ማተኮር፣ ለድርጅቶች መጠናከር፣ ማበርና መተማመን ፣ በተናጠል የሚደረገውን ትግል ማሰባሰብ ይቻልም ዘንድ አበራታች ለመሆን በሚያስችለን፣ በተሻለ ሁኔታ ተደራጅተናል::

ፋታን፣ ዋዘኛነትንና ለነገ ማሸጋገርን በማይጋብዘው በዚህ የሀገርና የህዝብ ጉዳይ ውስጥ እራስን የማስገኘት ግዴታ ውስጥ ተሳትፈን፣ የየችሎታችንንና የየብቃታችንን ልናዋጣ ያስችለናል በሚል እምነት፣ በስዊዘርላንድ ለሚኖሩ በፖለቲካ ድርጅትም ሆነ በድጋፍ ማህበራት ተደራጅተው ላሉ፣ በሲቪክ ማህበራትና በእምነት ተቋማት ስር ተሰባሰበው ለሚገኙ፣ በግል ላሉም ሆነ በግል ትውውቅም ከሚገናኙ የሀገር ልጆች ጋር በአንድ ላይ ሆነን በአካባቢያችን የተማከለና አንድ ወጥ እንቅስቃሴ ልናደርግ እንችል ዘንድ፣ በጋራ የሚያገናኘን **መድረክ** እየፈለግን ነው::

መልዕክታችን የኛን በተሻለ ተደራጅተን፣ በጋራ ለመስራትም ዝግጁ ሆነን መገኘታችንንና ማህበራችንን “የህብረት ድጋፍ ማህበር በስዊዘርላንድ“ (ህድማስ)ን ለማስተዋወቅ ሲሆን በተከታይ መልዕክቶቻችን በስዊዘርላንድ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ፣ በስዊዘርላንድ ላሉ  የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች፣ ግንባሮች፣ ቅንጅቶች፣ ስብስቦች፣ ህብረቶች፣ ወዘተ.. አካላት፣ ቅርንጫፎች እና ድጋፍ ማህበራት/ኮሚቴዎች፣ ለሲቪክ ማህበራት፣ ለዕምነት ማህበራት ፣ ሁሉን ሊያሰባስብ፣ ሊያሳትፍና ሊያስተባብር የሚችል የጋራ መድረክ ምስረታ ጥሪ እንደምናደርግ በቅድሚያ ለማስታወስ ነው::

አስተያየትዎንና መልዕክትዎን በተስፋ እንጠባበቃለን::

## ኢትዮጵያ ልጆቹዋን ትጣራለች።

**ከአክብሮት ሠላምታ ጋር**

**የህብረት ድጋፍ ማህበር በስዊዘርላንድ ( ህድማስ )**
**የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ**

**ለግንኙነት በዚህ  አድራሻ ይጠቀሙ:-**


**ለፖስታ መልዕክት**
Association Suisse de Soutien à l`Union
des Forces Démocratiques Ethiopiennes (ASSUFDE)
Case Postale 274
1211 Geneve 4
uedf.swiss@yahoo.com

**ለቴሌፎን ግንኙነት**
079 410 92 57
079 368 48 45